# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የውጭ አቅራቢዎች ሸቀጦችን ከውጭ ስለሚያስገቡበት አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 250/2013

ነሐሴ 2012 ዓ/ም
ገንዘብ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

# የውጭ አቅራቢዎች ሸቀጦችን ከውጭ ስለሚያስገቡበት
# አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 250/2013

እያደገ የመጣውን ሸቀጦች የዋጋ ግሽበት እንዲቀንስ ብሎም ለህብረተሰቡ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ ለማድረግ፤

ሀገራችን ለጊዜው የገጠማትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመቋቋም መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ በልዩ ሁኔታ ለማስገባትና ለማሰራጨት እንዲያስችል በማሰብ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመግዛት የተለዩ እና የሚለዩ ሸቀጦችንና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደአገር ውስጥ ለማስገባት እንዲችሉ የገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ እንዲያወጣ ጥር 19 ቀን 2012 ዓ/ም በቁጥር-መ30-5/732 በተፃፈ ደብዳቤ ውክልና የሰጠ በመሆኑ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የውጭ አቅራቢዎች ሸቀጦችን ከውጭ ስለሚያስገቡበት አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 250/2013 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

1/ "ሸቀጦች" ማለት የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመጠቀም ወደሀገር ውስጥ የሚያስገቧቸውን በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ይጨምራል፤

2/ "የውጭ አቅራቢ" ማለት ሸቀጦችን ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ተጠቅመው በዘገየ ክፍያ ለማቅረብ የመወዳደሪያ ሀሳብ ካቀረቡት መካከል በዚህ መመሪያ መስፈርት መሰረት ተመርጠው ከሚኒስቴሩ ጋር ውል የሚዋዋሉ የውጭ ድርጅቶች ናቸው፤

3/ "አከፋፋዮች" ማለት ሸቀጦችን ከውጭ አቅራቢ ገዝተው በሀገር ውስጥ ለማከፋፈል በሚኒስቴሩ የተመረጡ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ናቸው፤

4/ "ልዩ ፈቃድ" ማለት በሚኒስቴሩ ለውጭ አቅራቢዎች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

5/ "ቴክኒካል ኮሚቴ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 የተጠቀሱትን ተግባራት እና ኃላፊነት እንዲያከናውን በዚህ መመሪያ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

6/ "የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የሚፈጸሙ ግዥዎችን መርምሮ የሚያፀድቅ በሚኒስትሩ የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

7/ "ሚኒስትር እና ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር እና ሚኒስቴር ነው፤

8/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በዚህ መመሪያ በተደነገጉ ሸቀጦች ግብይት በሚፈጽሙና በሚያስፈጽሙ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ ሀገሪቱ የገጠማትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቋቋም እንዲያግዝ የውጭ አቅራቢዎች የራሳቸውን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ተጠቅመው በማስገባት የተለዩ/የሚለዩ ሸቀጦችን ከውጭ በማቅረብ በልዩ ሁኔታ ተሳታፊ የሚሆኑበትን አሰራር ማዘርጋት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

5. **የገንዘብ ሚኒስቴር**

1. በሚኒስቴሩ፣ በውጭ አቅራቢዎች፣ አከፋፋዮች መካከል የሚደረገው ግንኙነት በፅሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲሆን ያደርጋል፤
2. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የሚውል የፈቃድ ሰነድ፣ በአከፋፋይና በውጭ አቅራቢ መካከል የሚደረግ የሽያጭ ውል፣ የውል ሰነድ እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶችን ያዘጋጃል፡፡

6. **የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት ወደሀገር ወስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን ዓይነት እና መጠን ይወስናል፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ለአንድ ሸቀጥ የሚመረጡት የውጭ አቅራቢዎች ብዛት ከሁለት ያነሰ ሊሆን አይችልም፤

3/ በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት የሸቀጥ ዓይነቶች በተጨማሪ በውጭ አቅራቢዎች ወደሀገር የሚገቡ ሸቀጦችን ዓይነት ሊወስን ይችላል፤

4/ በዚህ መመሪያ መሰረት ከአሸናፊ የውጭ አቅራቢዎች ጋር ውል ይዋዋላል፣ የውጭ አቅራቢዎችን ከአከፋፋዮች ጋር ያዋውላል አፈፃፀሙንም ይከታተላል ፣ይቆጣጠራል፤

5/ የውጭ አቅራቢዎች ወደአገር ላስገቧቸው ሸቀጦች ከሚኒስቴሩ ጋር በገቡት ውል መሰረት ክፍያ የሚፈፀምበትን ጊዜና የክፍያውን መጠን የሚያሳይ ወይም የውጭ አቅራቢው ከዚህ የሚያገኘውን ጥቅም ሀገር ወስጥ የሚያውለው ከሆነ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ዝርዝር ሚጃውን ይልካል፤

6/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የሚያግዙ ኮሚቴዎችን ወይም አካላትን ያቋቁማል፤

7/ በዚህ መመሪያ መሠረት ሸቀጦች ግብይት ወስጥ ተሳታፊ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፤

8/ በዚህ መመሪያ መሰረት የውጭ አቅራቢው ከሚኒስቴሩ ጋር ለሚደረገው ውል የውል ሰነዱን ያዘጋጃል፤

9/ በዚህ መመሪያ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛል፣ ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያስተላልፋል፤

10/ ለውጭ አቅራቢዎች ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፤

11/ የፍላጎት መግለጫ እንደአስፈላጊነቱ ሊያወጣ ይችላል፤

12/ ለሚደረገው ግዢ በቂ ተወዳደሪ ሊገኝ ይችላል ተብሎ ከታሰበ በቀጥታ የማወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ በማውጣት የማወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ በማላክ ጨረታ ያወጣል፤

13/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም እንደአስፈላጊነቱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

14/ በዚህ መመሪያ መሠረት በሚፈጽሙት ድርጅቶች ላይ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው መሰረት እርምጃዎች ይወስዳል፣ እንደአስፈላጊነቱም ሌሎች ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

15/ ሌሎች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 7. <u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ</u>

1/ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚቀርብለት መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለውጭ አቅራቢዎች ሊተላለፍ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ በወቅቱ እንዲልክ ይፈቅዳል፤

2/ አከፋፋዮች ከውጭ አቅራቢዎች ለገዟቸው ሸቀጦች በብር ለሚፈፅሙት ክፍያ በውጭ አቅራቢዎች ስም የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ያደርጋል፤

3/ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲያጋጥም ባለው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲፈታ ያደርጋል፤

4/ የውጭ አቅራቢዎች በንግድ ባንክ በተከፈተው ሂሳባቸው ለስራ ማስኬጃና ኢንቨስት ለሚድረግና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ወጪዎች በሚያቀርበው ሰነድ መሰረት ክፍያ እንዲፈፀም ይፈቅዳል፤

5/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚመነጩ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 8. <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

1/ ሸቀጦችን ወደሀገር በማስገባት ከሽያጩ የሚገኙትን ገቢ ሚልሶ ለውጭ ዜጎች በተፈቀደ ማስክ ላይ ለኢንቨስትመንት ለማዋል ለሚፈልጉ የውጭ አቅራቢዎች ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚጣጣሙ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 9. የገቢዎች ሚኒስቴር

1/ የውጭ አቅራቢዎች ወደሀገር በሚያስገቧቸው ሸቀጦች ላይ የጉምሩክ ፎርማሊቲ በፍጥነት እንዲፈፀም ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

2/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ከተግባርና ኃላፊነቱ የሚጣጣሙ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 10. የቴክኒካል ኮሚቴ አደረጃጀት

1. የቴክኒካል ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ) ከሚኒስቴሩ የኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ እና ሁለት አባላት፤

   ለ) ከማንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ምክትል ሰብሳቢ፤

   ሐ) ከገንዘብ ሚኒስቴር ሁለት አባላት፤

   መ) ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት አንድ አባል እና፤

   ሠ) ከትራንስፖርት ሚኒስቴር አንድ አባል ይይዛል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ እንደአስፈላጊነቱ በጉዳዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ተቋማትን ወይም ግለሰቦችን በአስረጂነት ወይም በሙያዊ ተዋዕፆ እገዛ እንዲያደርጉ ሊምድብ ይችላል፤

3/ ሚኒስቴሩ እንደአስፈላነቱ የሥራ ክፍል በሚቋቋም የኮሚቴውን የሥራ ጊዜ እንዲያበቃ ሊያደርግ ይችላል፣

## 11. የቴክኒካል ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

የመወዳደሪያ ሐሳብ ማጠየቂያ ማስታወቂያ ያወጣል፣ ያወዳድራል፣ ይመርጣል፣ ሲፀድቅም ወጤቱን ያሳውቃል፣ሌሎች አስፈላጊ ተያያዥ ጉዳዮችን ያከናውናል፡፡

## 12. የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

በሚኒስትሩ የሚቋቋመው የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ፡ -

1/ በዚህ መመሪያ የሚፀሙ ግዥዎች ማስረታዊ የግዥ ሕግ መርሆችን ተከትሎ የተከናወነ/የተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

2/ በቴክኒካል ኮሚቴው የቀረቡ የጨረታ ወይም የግዥ ግምገማ ሪፖርቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

3/ በዚህ መመሪያ ማስረት የሚፀሙ ግዥዎች ወጤታማ ለሚድረግ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ሚኒስትሩን ያማክራል፣ የወሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

## 13. የአከፋፋይ ተግባራትና ኃላፊነት

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት በሚኒስቴሩ ከተሚጡ የውጭ አቅራቢዎች ጋር ሸቀጦችን ለመግዛት ወል ከሚፈራረሙ በፊት ለግዢው የሚያስፈልገውን የክፍያ ገንዘብ በሀገር ወስጥ ባንክ ተቀማጭ ሚድረግ አለበት፤

2/ አከፋፋዩ በፈጸመው ወል መሠረት ከውጭ አቅራቢው የገዛውን ሸቀጦችን ሲረከብ፣ ሚከቡን ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 14. የውጭ አቅራቢ ኃላፊነትና ግዴታ

የውጭ አቅራቢው ሞልቶ በሚያቀርበው የመወዳደሪያ ሐሳብ ማጠየቂያ እና በሚፈጽመው ወል የሚለጹ ዝርዝር ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1/ የሚያቀርባቸው መሠረታዊ ሸቀጦች የኢትዮጵያ ደረጃን ያሟሉ መሆን አለባቸው፤

2/ የሚያቀርባቸው ሸቀጦችን የማጠብት ሀገር ሚረጋገጫ የአምራች ድርጅት ሥም፣ ደረሰኝ እና ተያያዥ ዝርዝር ሰነዶች ምርቶቹን ወደሀገር ወስጥ ከማስገባቱ በፊት ማቅረብ አለበት፤

3/ የሚያቀርባቸው ሸቀጦችን በአጫጫኑ፣ በአስተሻሸግ ፣ በጥራት ጉድለት እና ማሳል ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለሚፎር ተጠያቂነት ሙሉ ኃላፊነት አለበት፤

4/ የጨረታ እና የወል ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ አለበት፤

5/ ለሸያጩ ክፍያው የሚጸምበት ጊዜን እና ከሽያጭ ያገኘው ገንዘብ ወይም ገቢ አጠቃቀምን በተማለከተ አሸናፊ ለማሆን ባበቃው ማስፈርት መሠረት ሚፈጸም አለበት፡፡

## 15. ወደ አገር የሚገቡ ሸቀጦች ስለሚሰራጩበት ሁኔታ፣

በዚህ መመሪያ መሠረት ወደሀገር ወስጥ የሚገቡ ሸቀጦች በሀገር ወስጥ የሚሰራጩት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡-

1/ የመሠረታዊ የንግድ ዕቃዎች ለህብረተሰቡ ለማሰራጩት ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 02/2008ዓ/ም፣

2/ የምግብ ዘይት አቅርቦትና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 020/2011ዓ/ም፣

3/ ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የሸቀጥ ዓይነቶችና የውጭ <u>አቅራቢዎችን የማሪጫ ማስፈርት</u>

### 16. <u>የሸቀጥ ዓይነቶች</u>

ሀ) ስንዴ
ለ) የምግብ ዘይት
ሐ) ስኳር
መ) ሩዝ
ሠ) በሂደት ሊምጡ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ግብአቶች እና ሌሎች ሸቀጦች

### 17. <u>በአከፋፋይነት ስለማሪጥ</u>

1/ በአከፋፋይነት የተሚጡት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው፡ -

ሀ/ የስኳር ምርትን ለማከፋፈል የስኳር ኮርፖሬሽን፤

ለ/ የዳቦ ስንዴና ሩዝን ለማከፋፈል የንግድ ሥራ ኮርፖሬሽን፤

ሐ/ የምግብ ዘይትን ለማከፋፈል የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት እና የንግድ ሥራ ኮርፖሬሽን (አለበጅምላ) እና

መ/ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ለማከፋፈል የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት፤

ናቸው፡፡

2/ በውጭ አቅራቢዎች ወደሀገር ውስጥ እንዲገቡ በሚኒስቴሩ የሚወሰኑ ሌሎች ሸቀጦችን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሱት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተጨማሪ ሌሎች የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአከፋፋይነት ሊሚጡ ይችላሉ፡፡

### 18. <u>የግንኙነት ስልት</u>

በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 26(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚኒስቴሩ እና በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች ለዚሁ ተግባር አገልግሎት የሚሰጥ በኮሚቴው አባላት በጋራ ኮድ ብቻ የሚከፈት በማሰሪያ ቤቱ ብቻ የሚተዳደር የኢ-ሜል

አድራሻ ሲሆን በዚህ የኢ-ሜል አድራሻ የሚደረግ የሚጀ ልውውጥ ትክክለኛነቱ እና በሚስጥር ማጠበቁን ሚረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፤

19. <u>የመወዳደሪያ ሐሳብ ማጠየቂያ ስለሚከበት እና አሸናፊ የውጭ አቅራቢዎች ስለሚሚጠዑት ሁኔታ</u>

1/ ለውጭ አቅራቢዎች የመወዳደሪያ ሐሳብ ማጠየቂያ ሰፊና ተደራሽነት ባለው የግንኙነት ዘዴ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል፤

2/ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ጥሪ ከ35 እስከ 45 ተከታታይ ቀናት ይቆያል፣

3/ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ላይ የማብራሪያ ጥያቄ ያላቸዉ የውጭ አቅራቢዎች ጥያቄያቸውን ማቅረብ የሚችሉት የመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ጥሪ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት ወስጥ ብቻ ሊያቀርቡ ይችላሉ፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ላይ ለሚቀርብ ተጨማሪ የማብራሪያ ጥያቄ ጥያቄው በቀረበ በአምስት ቀናት ወስጥ ምላሽ ማስጠት አለበት፤

5/ የውጭ አቅራቢዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ምላሽ ግዥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ማሰረት በጋራ በተከፈተው የኢ-ሜል አድራሻ አካውንት መላክ አለባቸው፤

6/ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ ጥሪ የጊዜ ገደብ ካበቃበት ቀን ቀጥሎ ባለው የሥራ ቀን ኮሚቴው ተሳታፊ የውጭ አቅራቢዎች በአካል ወይም በኦንላይን በተገኙበት ሰነዱን ይከፈታል፤

7/ የመወዳደሪያ ሐሳብ ማጠየቂያ ምላሻቸውን የላኩ የውጭ አቅራቢዎች ከሦስት በታች ከሆኑ ሂደቱ ይሰረዛል፣

8/ አሸናፊ የውጭ አቅራቢዎች ሸቀጦችን ወደአገር ወስጥ በማስገባት ለአከፋፋዮች ለሽያጭ የሚያቀርቡ መሆኑን፣ ክፍያው የሚጸምበት ጊዜን እና ከሽያጭ ያገኙትን ገንዘብ ወይም ገቢ አጠቃቀምን በተመለከተ አሸናፊ ለመሆን ባበቃቸው ማስፈርት መሠረት የሚፈጽሙ መሆኑን በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚኒስቴሩ ጋር ወል እንዲፈጽሙ ይደረጋል፣

9/ አሸናፊ የውጭ አቅራቢዎች በዚህ መመሪያ መሠረት ከአከፋፋዮች ጋር የሸቀጦች የሽያጭ ወል እንዲፈጽሙ ይደረጋል፡፡

20. <u>ልዩ ፈቃድ ስለማስጠት</u>

1/ አሸናፊ በመሆን የተመረጡ በዚህ መመሪያ መሰረት ወል ለሚፈፅሙ የውጭ አቅራቢዎች ሚኒስቴሩ ልዩ ፈቃድ ይሰጣቸዋል፤

2/ ሚኒስቴሩ በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው የመንግሥት አካላት የሚከተሉት ፈቃዶች ለአቅራቢዎች እንዲሰጡ ድጋፍ ያደርጋል:-

ሀ) ሸቀጡን ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ወደሀገር ወስጥ እንዲያስገቡ ለጉሙሩክ ኮሚሽን፤

ለ) በስማቸው የባንክ አካውንት እንዲከፍቱ

ሐ) በራሳቸው የሚጓጓዣ እንዲጠቀሙ ለኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት

## 21. ማስፈርት

በመወዳደሪያ ሀሳብ ማጠየቂያ መሰረት ለወድድር ከሚቀርቡ የውጭ አቅራቢዎች መካከል አሸናፊው የሚሚጠው ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው የሚወዳደሪያ መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 22. በምልማና ሚጣ ሂደት ላይ የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ስርዓት

1/ ማንኛውም የውጭ አቅራቢ፣ አከፋፋይ፣ ቀጥተኛ ገዢ እርሱን በተመለከተ ወሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ ላይ ቅሬታ ካለው ወሳኔው በተሰጠ በአምስት የሥራ ቀናት ወስጥ ቅሬታውን ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፣

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የቀረበለትን ቅሬታ፣ ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ አስር ቀናት ወስጥ ጉዳዩን በማጣራት ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ምላሽ ማስጠት አለበት፡፡ ምላሽ ካልተሰጠው ወይም የተወሰነው ወሳኔ ካጸናው ይግባኙን ለሚደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 23. ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች

1/ የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በማጠቀም በመንግስት የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደሀገር ወስጥ የሚያስገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 62/2012 በዚህ መመሪያ ተሸሯል፤

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ተለምዶዊ አሰሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**24. መመሪያውን ስለማሻሻል**

የገንዘብ ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሻል ወይም ሊሽር ይችላል፡፡

**25. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 1 ቀን 2012 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ነሐሴ 01 ቀን 2012 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

**የሚወዳደሪያ መስፈርት እና ክብደት ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | መስፈርት | ክብደት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | የፋይናንስ አቅም መግለጫ (ኦዲት ሪፖርት) | 5% | ለከፍተኛ የፋይናንስ አቅም 5% የሚያገኝ ሲሆን ለተቀሩት በሚቀርቡት የፋይናንስ አቅም ማስረት ተሰልቶ ውጤታቸው ይሜዛናል፡፡ |
| 2 | በዘርፉ ያለ የሥራ ልምድ | 5% | በቀጥታ በስራው ላይ የተሰማሩና በስራው ባሳለፉት ጊዜ ማስረት ተሰልቶ ውጤታቸው ይሜዛናል፡፡ |
| 3 | ከሽያጭ የሚገኘው ገቢ አጠቃቀም | 45% | |
| | 3.1 ከሽያጭ ገቢው ከ50 -100% | 25% | ለከፍተኛ መቶኛ ሙሉ ክብደት ለዝቅተኛ መቶኛ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ኢንቨስትመንት ላይ ማዋል | | በቀጥታ የተገናኘ ተመጣጣኝ (proportional) ክብደት ማስጠት |
| | 3.2 የተወሰነ መኖኛ ድርሻ ኢንቨስትመንት ላይ ማዋል<br>3.2.1 ከሽያጩ 10% - 19%<br>3.2.2 ከሽያጩ 20% - 29%<br>3.2.3 ከሽያጩ 30% - 39%<br>3.2.4 ከሽያጩ 40 ≤ X < 50% | <br><br>2.5%<br>5.0%<br>7.5%<br>10% | |
| | 3.3 ወደ ውጭ ማላክ (repatriate)<br>▪ ከ2 ዓመት በኋላ<br>▪ ከ3 ዓመት በኋላ<br>▪ ከ4 ዓመት በኋላ<br>▪ 5 እና ከ5 ዓመት በላይ | <br>2.5%<br>5.0%<br>7.5%<br>10 % | ለረጅም ወደውጭ የማላኪያ ጊዜ ከፍተኛ፣ ለአነስተኛ ጊዜ ደግሞ በቀጥታ የተገናኘ ተመጣጣኝ (proportional) ክብደት ማስጠት |
| 4 | የመሸጫ ዋጋ | 40% | ለዝቅተኛ ዋጋ ሙሉ ክብደት፣ ለከፍተኛ ዋጋ በቀጥታ የተገናኘ ተመጣጣኝ (proportional) ክብደት ማስጠት |
| 5 | ሸቀጦችን ሀገር ወስጥ ለማስገባት የሚወስደው ጊዜ | 5% | |
| | **ድምር** | **100%** | |